# በፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
# የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
# ዜና ኢ.ሕ.ጤ.ኢ.

ታህሳስ 2008 ቅጽ 1 ቁጥር 3

በኢ.ሕ.ጤ.ኢ. የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ቢሮ በየወሩ የሚዘጋጅ


## በባህላዊ መድሐኒት ዙሪያ አውደ ጥናት ተካሄደ



የኢንስቲትዩቱ ባህላዊ እና ዘመናዊ መድሐኒት ምርምር ዳይሬክቶሬት ስለ ባህላዊ መድሐኒት ቀደም ሲል ስለተከናወኑት፣ በአሁኑ ጊዜ በመከናወን ላይ ስላሉትና የወደፊት አቅጣጫዎች ላይ ያተኮረ አውደ ጥናት ከታህሳስ 4-6/2008 በአዳማ ከተማ አካሄደ።

በባህላዊ መድሐኒት ላይ የተሰሩ የምርምር ውጤቶችን ማሳወቅ በውጤቶቹም ላይ ያለውን ደካማ እና ጠንካራ ጎኖች ላይ መወያየት፣ እንዲሁም ያሉትን ተግዳሮቶች በማስወገድ በቀጣይ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ባሕላዊ መድሐኒቶች ላይ የሚሰሩ ተቋሞች ጋር በትብብር የሚሰራበትን ሁኔታ ማመቻቸት የአውደ ጥናቱ ዋና ዋና አላማዎች ነበሩ።

የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ይበልጣል አሰፋ በመክፈቻ ንግግራቸው እንዳመለከቱት አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ባህላዊ መድሐኒቶችን የሚጠቀም ሲሆን ዋናው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ግን ባህላዊውን ከዘመናዊው መድሐኒት ማጣመር መቻል መሆኑን ጠቁዋል።

በአውደ ጥናቱ ላይ የተለያዩ የምርምር ውጤቶች ከቀረቡ በኋላ የባሕላዊ መድሐኒቶች ላይ የሚሰሩ የምርምር ስራዎች የሚታዩ ክፍተቶች ላይ የቡድን ውይይት ተደርጎባቸው ወደፊት መሆን ስላለበት አዎንታዊ ሀሳቦች ቀርበዋል። በተጨማሪም ከሀገር ውስጥ መድሐኒት አምራቾች ጋር በተቀናጀ መልኩ እንዴት መስራት እንደሚቻል እና የባሕላዊ መድሐኒት ቁጥጥር ላይ ከመንግስት አ

. . .ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## በኤች.አይ.ቪ. እና ተያያዥ በሽታዎች ላይ ያተኮረ አውደ ጥናት ተካሄደ




ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የፌደራል ኤች.አይ.ቪ. መከላከያና ቁጥጥር ጽ/ቤት እና ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመሆን ኢንስቲትዩቱ በአዋሳ ከተማ ከህዳር 30 እስከ ታህሳስ 2/2008 በኤች.አይ.ቪ. እና ተዛማጅ በሽታዎች ላይ በተካሄደ የዳሰሳ እና የቁጥጥር ጥናት ላይ አውደ ጥናት አካሄደ፡፡

እንደ አውደ ጥናቱ አዘጋጆች አውደ ጥናቱ አጋር ድርጅቶችን በኢትዮጵያ ኤች.አይ.ቪ. ወረርሽን በተመለከተ ያለውን ወቅታዊ ሁኔታ ለማሳወቅ፣ የምርምር ውጤት ግኝቶችን ለመጋራትና ወሳኝ የዳሰሳ እና የቁጥጥር ግኝቶችን ለማሳወቅ፣ ያሉትን የመረጃ ክፍተቶች ለመለየት እና ለመጪው የፈረንጆች ዓመት የተሻሉ አካሄዶችን ለማስቀመጥና ከዓለም ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ያሉ አቅጣጫዎች ላይ ለመወያየት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ሲ/ር ፍቅርተ አበራ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጤና ቢሮ የበሽታ መከላከልና ቁጥጥር ዳ

. . .ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የጊኒ ትል በሽታን ለማጥፋት በሚካሔዱ መርሀ ግብሮች ላይ ውይይት ተካሄደ




ኢንስቲትዩቱ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከጋምቤላ ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ፣ ከካርተር ማዕከል እና ከዓለም የጤና ድርጅት ጋር በመተባበር የጊኒ በሽታን ለማጥፋት በመካሄድ ላይ ያሉትን መርሀ ግብሮች ለመከለስ እና ለመወያየት ከታህሳስ 4-5/2008 በጋምቤላ ከተማ የግምገማ ስብሰባ አካሂዷል።

ስብሰባውም ባለፈው የፈረንጆች አመት በእያንዳንዱ ወረዳ የተገኙ ውጤቶችን መተንተን፣ ከዚህ በፊት የተሰጡ ማሳሰቢያዎች ምን ያክል ተፈፃሚ እንደሆኑ መገምገም፣ ካለፈው ዓመት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን በመለየት ለመጪው አመት የሚስተካከሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ የመጪው ዓመት እቅድ ላይ መወያየት፣ የበሽታውን ስርጭት ለመግታት መንገዶችን ማስቀመጥ እና በሽታው ሙሉ በሙሉ መወገዱ የሚረጋገጥበት አቅጣጫን ማስቀመጥ ዋና ዋና ዓላማዎች ነበሩ።

የጋምቤላ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝደንት አቶ ጋትሉዋክ ቱብ በመክፈቻ ንግግራቸው የጊኒ ትል በሽታን ከጋምቤላ ለማጥፋት ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና አጋር ድርጅቶች ጋር የምንሰራበት ወቅት መሆን አለበት ሲሉ ተናግረዋል።

የተከበሩ የዓለም ሎሬት እና አፍሪካን በመወከል በኢትዮጵያ የጊኒ ትል በሽታን የማጥፋት መርሀ ግብር የበጎ ፈቃድ አምባሳደር የሆኑት ዶ/ር ጥበበ የማነ ብርሃን በበኩላቸው የጊኒ ትል በሽታን ከጋምቤላ ክልል እንዲሁም ከኢትዮጵያ በመጪው ዓመት ሙሉ ለሙሉ ለማጥፋት በጋራ በመሆን ጠንክረን መስራት አለብን ብለዋል።

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር አምሐ ከበደ በበኩላቸው በመጪው የፈረንጆች ዓመት የጊኒ ትል በሽታን ከጋምቤላ ጨርሶ ለማጥፋት የኢትዮጵያ መንግስት በተጨማሪም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ቀኝ እጅ የሆነው የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በቁርጠኝነት እንደሚሰሩ አስታውቀዋል።

የካርተር ማዕከል ተወካይ በበኩላቸው ማዕከሉ ላለፉት 30 አመታት በኢትዮጵያ በሽታውን ለማጥፋት ሲሰራ የቆየ መሆኑንና ወደፊትም ይህንኑ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።


በውይይቱ ላይም የጋምቤላ ክልላዊ መንግስት፣ የስደተኞች መጠለያ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የጊኒ ትል በሽታን የማጥፋት ፕሮግራሞች የስራ አፈጻጸም ሪፖርቶች ቀርበዋል። በተጨማሪም በጋምቤላ በሽታውን ለማጥፋት የጤና ኤክስቴሽን ባለሞያዎች ሚና የቀረበ ሲሆን የባለፈው የፈረንጆች ዓመት በሽታውን ለማጥፋት የዓቅርቦት እና የምዝገባ ሒደቶች ሪፖርት ከቀረበ በኂላ በዚሁ ላይ ውይይት ተካሒዶበታል።

በአጠቃላይ በውይይቱ ላይ 16 ገንቢ ሃሳቦች የቀረቡ ሲሆን ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከጋምቤላ ክልላዊ መንግስት የጤና ቢሮ፣ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጤና ቢሮ፣ ከካርተር ማዕከል፣ ከዓለም ጤና ድርጅት እንዲሁም ከኢንስቲትዩቱ የተውጣጡ ከ170 በላይ ተሳታፊዎች በውይይቱ ተገኝተዋል።

# የኢንስቲትዩቱ ተማራማሪ ባለሙያዎች ጨው ን በአይዎዲን የማበልጸጊያ ቀላል ማሽን ሰሩ

ስነ-ምግብ ላይ ምርምር የሚያደርጉ
ት የኢንስቲትዩቱ ተመራማሪ ባለሞ
ያዎች ወደ ኢንዶኔዢያ ሃገር በመሄ
ድ፣ ልምድ በመቅሰም እና በማጥና
ት ለሃገራችን ጠቃሚ የሆነ ጨውን
በአዮዲን የማበልጸጊያ መሳሪያ ለሃገ
ራችን በሚመች መንገድ በማሻሻል
ቀላል ማሽን መስራት ቻሉ።
አቶ ተስፋዬ ሐይሉ የምግብ ሳይንስ
ና ስነ-ምግብ ምርምር ዳይሬክቶሬት
ተጠባባቂ ዳይሬክተር  የተሻሻለውን
ቀላል ማሽን አስመልክቶ እንደገለጹ
ት በአሁኑ ሰአት የተለያዩ ከስርዓተ
ምግብ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የ
ንጥረ-ምግብ ዳሰሳ ጥናቶች ተሰርተ
ዋል።ዋና አላማውም በንጥረ ምግብ
የበለፀገ ምግብ ለህብረተሰቡ ማድረ
ስ ነው።ከዚህም ውስጥ ጨውን በአ
ዮዲን አበልጽጎ ለህብረተሰቡ የማዳ
ረስ ስራ በከፍተኛ ሁኔታ እየተሰራ
ይገኛል፤ይህ ደግሞ በአዮዎዲን እጥረ
ት ምክንያት በህብረተሰቡ ላይ የሚ
ፈጠረውን የእንቅርት በሽታ ከመቀ
ነሱም በላይ የህጻናትን ንቃተ ህሊና
ከፍ ያደርጋል ብለዋል።
ዳይሬክተሩ አያይዘው እንደተናገሩ
ት የኢንስቲትዩታችን ተመራማሪ ባ
ለሙያዎች ኢንዶኔዥያ ሃገር በመሄ
ድ ለህብረተሰቡ የሚጠቅም ልምድ
በመቅሰምና በማጥናት ጨውን በአ
ዎዲን የማበልጸጊያ ቀላል ማሽን ሰ
ርተዋል።ጥቅሙም የአዮዲን እጥረት
ባለባቸው ክልሎች ጨውን በአዮዲ
ን እንዲበለጽግ የሚያደርግ ሲሆን
ለጨው አምራቾችም ከፍተኛ ጥቅ
ም ይሰጣል ካሉ በኋላ በቀጣይም የ
ኢንስቲትዩቱን የላብራቶሪ አቅም በ
መገንባት የየክልሎችን ላብራቶሪ አ
ቅም በመፈተሽ የአቅም ግንባታ ስ
ራ ይሰራል፤ምርምሩንም አለም አቀ
ፍ ተቀባይነት እንዲኖረው ይደርጋ
ል ብለዋል።
ዳይሬክተሩ ቀጥለው እንደተናገሩት
በቀጣይ ኢንስቲትዩቱ ምርምሩን በ
ማስፋት በሃገር አቀፍ ደረጃ የተሰራ
ጨውን ጨው በመፈተሽ ለሚመለ
ከተው አካል ያቀርባል ብለዋል።
በመጨረሻ ዳይሬክተሩ እንዳስቀመ
ጡት ለቀላል ማሽኑ ቴክኖሎጂ እዚ
ህ ላይ ደርሶ የተሳካ ስራ እንዲሰራ
የገንዘብ ድጋፍ ያደረገው የማይክሮ
ኒውትረንት ኢኒሼቲቭ ድርጅት መ
ሆኑን ገልጸዋል።

# የኢንስቲትዩቱ የሴቶች እና ወጣቶች ጉዳይ ዳይ ሬክቶሬት ስረአተ ጾታን አስመልክቶ ስልጠና ሰጠ



የኢንስቲትዩቱ የሴቶች እና ወጣቶ
ች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት በስርዓተ ጾ
ታ ጽንሰ ሐሳብ፣ከስረአተ ጾታ ጋ
ር የተያያዙ ህጎች እና ስነ-ምግብ
ን አስመልክቶ ያዘጋጀውን የግንዛ
ቤ ማስጨበጫ ስልጠና ከታህሳስ
21-23/2008 ዓ.ም በኢንስቲትዩቱ
አዳራሽ ከዚህ በፊት ስልጠናውን ላ
ልወሰዱ የተቋሙ ሰራተኞች ስልጠ
ና ሰጠ።
ወይዘሮ ሙኒት መኩሪያ  የስረአተ
ጾታ ከፍተኛ ባለሞያ የስልጠናውን
ዋና አላማ አስመልክቶ እንደገለጹ
ት ይህ ስልጠና ስርዓተ ጾታ ከህግ
ጋር ያለውን ግንኙነት ለማስገንዘብ
ሲሆን የሴቶችን መብት ከሃገር አቀ
ፍና ከአለም አቀፍ ህጎች ጋር ያለ
ውን ግንኙነት ለማሳወቅ ብሎም የ
ተሻሻሉ ህጎች ስለ ሴቶች ምን ይላ
ሉ የሚሉትን እና ጤናማ የአመጋገ
ብ ስርአት ምን እንደሚመስሉ ለማ
ስጨበጥ ታስቦ የተዘጋጀ ስልጠና ነ
ው ብለዋል።
ባለሞያዋ አያይዘው እንደገለጹት ስ
ልጠና የግንዛቤና የአመለካከት ለው
ጥ የሚያመጣ ስለሆነ ስረአተ ጾታ
ን በተመለከተ በምርምሩም ዘርፍ
ሆነ በማንኛውም የኢንስቲትዩቱ እ
ንቅስቃሴ ላይ በማካተት የተዛባው
ን የስረአተ ጾታ አመለካከት ወደ ት
ክክለኛው መንገድ በማምጣት እንደ
ዳይሬክቶሬታችን ትልቅ መሻሻል ይ
ፈጠራል  ብለን እናምናለን ሲሉ ተ
ናግረዋል።
አቶ ተዘራ ወ/መድህን የግል አማ
ካሪ ስለ ስልጠናው ጠቃሚነት ሲ
ያስረዱ እንዳስቀመጡት በዚህ ስል
ጠና ወቅታዊ የሆነውን በሴቶች ላ
ይ እየደረሰ ያለውን አስቸጋሪ ሁኔ
ታ፣ስርዓተ ጾታን በተመለከተ የተዘ
ረጉ እድሎችንና የስርዓተ ጾታን ም
ንነት በሚገባ እንገነዘባለን በማለት
ገልጸዋል።
በሌላ  በኩል ወይዘሮ ትግስት ዘለ

. . .ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ከገጽ 1 የዞረ

. . .በባህላዊ መድሐኒት

ካል ጋር አብሮ የሚሰራባቸው ሁኔታዎ
ች በውይይቶቹ ከተነሱ ነጥቦች ጥቂቶ
ቹ ናቸው።
ከዩኒቨርሲቲዎች የመጡ ተመራማሪዎ
ች፣ የባህል መድሐኒት አዋቂዎች እና የ
መድሐኒት አምራቾች በዓውደ ጥናቱ ላይ
የተሳተፉ ሲሆን ሁሉም ለዓውደ ጥናቱ
ጠቃሚ የሆኑ ግብዓቶች አቅርበዋል።

ከገጽ 1 የዞረ

. . ኤች.አይ.ቪ. እና ተያያዥ

ይሬክቶሬት ዳይሬክተር የቢሮውን
ሀላፊ በመወከል የእንኳን ደህና መ
ጣችሁ ንግግር ያደረጉ ሲሆን እን
ግዶቹም በአዋሳ መልካም ቆይታ
እንዲኖራቸው ተመኝተዋል፡፡
የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር
ዶ/ር አምሐ ከበደ በመክፈቻ ንግ
ግራቸው አውደ ጥናቱ ለሁሉም ባ
ለድርሻ አካላት ኤች.አይ.ቪ.ን በተ
መለከተ ወቅታዊ መረጃ የሚሰጥ
ሲሆን የሚቀርቡት የምርምር ጥና
ት ውጤት ግኝቶችም በሀገር አቀ
ፍ ደረጃ በሽታውን ለማጥፋት የ
ሚደረጉትን ጥረቶች እንደሚያግዙ
ጠቁመዋል፡፡
አቶ ብርሃኑ ፈይሳ ከፌደራል ኤ
ች.አይ.ቪ. መከላከያና ቁጥጥር ጽ/
ቤት፣ ዶ/ር አሸናፊ ሀይሌ የሲዲሲ
ኢትዮጵያ ተወካይ እና ዶ/ር ሚ
ርያም ማሌዋ የተባበሩት መንግስ
ታት እርዳታ ድርጅት ዳይሬክተ
ር በየበኩላቸው የመክፈቻ አድር
ገዋል፡፡
በአውደ ጥናቱ ላይ በብሔራዊና ክ
ልላዊ የኤች.አይ.ቪ. ስርጭትና መ
ጪ ሁኔታዎች ላይ የፓናል ውይ
ይት የተደረገ ሲሆን የኢንስቲትዩ
ቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር
ይበልጣል አሰፋ፣ አቶ ብርሃኑ ፈይ
ሳ የፌደራል ኤች.አይ.ቪ. መከላከያ
ና ቁጥጥር ጽ/ቤት ዋና ዳይሬክተር
ዶ/ር ፍሬህይወት ንጋቱ ከጤና ጥበ
ቃ ሚኒስቴር፣ ዶ/ር አሸናፊ ሀይሌ
ከሲዲሲ ኢትዮጵያ፣ ዶ/ር አላነካር
ማለቪያ ከተባበሩት መንግስታት
እርዳታ ድርጅት እና ዶ/ር ፍቃዱ
አዱኛ ከዓለም የጤና ድርጅት የፓ
ናሉ አቅራቢዎች ነበሩ፡፡

# ወቅቱን የጠበቀ የሰራተኞች የስራና የደንብ ልብስ ተሰጠ

በግዥና በተላያዩ ምክንያቶች ሲ
ጓተት የነበረውን የደንብ ልብስ ለ
ሰራተኞች የመስጠት የአሰራር ች
ግር በማሻሻል ለሰራተኖች ታህሳ
ስ 30 /2008 ዓ.ም የስራና የደን
ብ ልብስ እንደተሰጠ ተገለጸ፡፡
አቶ ታደሰ ንጋቱ ሰው ሃብት ስራ
አመራር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተ
ር እንደገለጹት በኢንስቲትዩቱ የ
ስራና የደንብ ልብስ በተለያዩ የስ
ራ ዘርፍ ለተሰማሩ ሰራተኞች ይ
ሰጣል፡፡ይህም በስራ ላይ እንደመ
ለያና በስራ ምክንያት በሚደረጉ
ንክኪዎች ከሚፈጠሩ የተለያዩ አ
ደጋዎች ለመከላከል ያገለግላል፡፡
ይሁን እንጂ ከዚህ በፊት የነበረ
ው የአሰጣጥ ሒደት በጣም የተጓ
ተተና ሰራተኛው ቅሬታ ያቀረበበ
ት ከመሆኑም በላይ በበጀት አመ
ቱ መጠናቀቂያ ወቅት በመሰጠቱ
ችግር ነበረው ብለዋል፡፡
ነገር ግን በዘንድሮው አመት የግ
ዥና ጠቅላላ አገልግሎት የስው ሃ
ብት ስራ አመራር ብሎም ከሰራ
ተኛው የተውጣጣ ኮሚቴ በማቀና
ጀት የነበረውን የተጓተተ አሰራ
ር በማሻሻል የሰራተኞችን የስራ
ና የደንብ ልብስ ወቅቱን በጠበ
ቀ መልኩ ለመስጠት ተችሏል፡፡
ይህም የሰራተኛውን የመስራት ተ
ነሳሽነት ከማሳደጉም በላይ የመል
ካም አስተዳደር ችግሮች እየተፈ
ቱ መሆናቸውን ያመልክታል ብ
ለዋል፡፡
ዳይሬክተሩ አያይዘው እንደገለጹ
ት ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ሰራ
ተኞች የደንብና የስራ ልብሱን ለ
ብሰው በስራ ላይ የመገኘቱ ጉዳ
ይ ችግር እየሆነ ነው ይህን ደግሞ
በቀጣይ የምናስተካክለው ይሆናል
ሲሉ ተናግረዋል፡፡
አቶ ጥበቡ በቀለ የጠቅላላ አገልግ
ሎት ዳይሬክቶሬት ጊዜዊ ዳይሬ
ክተር በበኩላቸው በአመቱ መጨ
ረሻ ይሰጥ የነበረው የስራና የደን
ብ ልብስ በያዝነው የበጀት አመ
ት ግን የተሻለ እቅድ በመታቀዱ
ና በቅንጅት በመሰራቱ የነበረው
ችግር ተቀርፎ ወቅቱን የጠበቀ ስ
ራ እንዲሰራና ሰራተኞች ቅሬታ
ቸውን እንዲቀርፉ ለማድረግ ተ
ችሏል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ከገጽ 3 የዞረ

. . ጾታን አስመልክቶ ስልጠና

ቀ ከኢትዮጵያ ሲት የህግ ባለሞያዎ
ች ማህበር የመጡ የህግ ባለሞያ ስ
ርዓተ ጾታን እስመልክቶ ከሃገራች
ን ህግ እና ከአለም አቀፍ ህግ ጋ
ር እያነጻጸሩ ትምህርቱን የሰጡ ሲ
ሆን የሴቶችን የበታችነት በኢትዮጵ
ያ ህጎች ታሪክ፣በኢካኖሚ፣በማህበራ
ዊ እና በስነልቦናዊ ሴቶች ላይ ይ
ደርስ የነበረውን ጫና ከማስረዳታቸ
ውም በላይ አሁን ሃገራችን እየተገበ
ረችው ያለውን የስረአተ ጾታ ህጎች
በፊት ከነበሩት ህጎች ጋር በማወዳደ
ር አብራርተዋል።
አቶ ተስፋዬ ሐይሉ የስነ-ምግብ ም
ርምር ዳይሬክቶሬት ተጠባባቂ ዳይ
ሬክተር ስነ-ምግብን በተመለከተ ጤ
ናማ የአመጋገብ ስረአት ምንነትና
ትኩረት አሰጣጥ ሂደት ላይ ሰፋ ያ
ለ ትምህርት ሰጥተዋል።
ስልጠናው ለኢንስቲትዩቱ 28 ተመ
ራማሪ ሰራተኞች፣ለ26 አስተዳደር
ሰራተኞች በአጠቃላይ ለ54 ሰራተኞ
ች ለሶስት ቀናት ተሰጥቷል።